# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 35

ጥቅምት 6 ቀን 2015ዓም(16-10-2022)

በዬሳምንቱ በምናቀርበው ያገር እንዴት ሰነበተች ቅንብራችን በአገራችን ውስጥ የተከሰቱትን የተለያዩ ሁኔታዎች በማንሳት ለማሳወቅና ብሎም የክስተቱ መነሻና ያስከተለውን ጉዳትም ይሁን የሰጠውን ጥቅም በሚመለከት አስተያዬትና ትችት ስንሰጥበት መቆዬታችንን ሁሉም የስርጭቱ ተከታታዮች እንደሚያውቁት እርግጠኞች ነን።

በዛሬውም ስርጭታችን እንዲሁ ባለፉት የአንድ ሳምንት ቀናት ውስጥ ተከስተው በሰፋት ትኩረት ስበዋል ባልናቸው ርዕሶች ላይ የበኩላችንን አስተያዬት የምንሰጥበት ይሆናል። ትኩረት ከተሰጠባቸውና ሕዝብ ከተነጋገረባቸው ውስጥ በአገራችን የፍትሕ አሠራር ምን እንደሚመስልና ውሸት ባሕል እዬሆነ መምጣቱን የሚያመላክቱ ድርጊቶች ዋናዎቹ ናቸው።

ፍትሕ ወይም ሕግ በአንድ አገር ውስጥ በሕዝብ ፍላጎትና ውሳኔ መንግሥታዊ ሥርዓት ሲሰፍን ለዚያ መንግሥታዊ ሥርዓት እንደ ጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያገለግል ዋናና ቀዳሚ ተቋም ነው።የመንግሥቱ ጸባይና ምንነት የሚታወቀው በሚመራበት የሕግ ደንብና ጥላ ሥር በሚከውነው የፍትሕ አሠራር ነው።ፍትሕና ሕግን መሣሪያው ያላደረገ መንግሥት መንግሥት ነው ተብሎ አይቆጠርም፤ በጉልበቱ አዳሪ፣ፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ ቡድን የሚፈነጭበትና ያሻውን የሚያደርግበት ስርዓትና ዘመን ሆኖ ይቆጠራል።

በእኛም አገር ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አገራት ካለሕዝቡ ፍላጎትና ምርጫ ሥልጣኑን በጉልበት ነጥቀው እራሳቸውን ከሕግ በላይ ያደረጉ ብቻ ሳይሆን እራሳቸው ሕግ የሆኑ አገዛዞች እዬወጡ እዬወረዱ ኖረዋል።አሁንም በእኛም አገር ጭምር የዚህ አይነት የወንበዴና ሕገወጥ ቡድን እራሱን በራሱ ሾሞ ያሻውን በማድረግ ብዙ ዓመቶች አልፈዋል፤ያሁኑም የጎሰኞች ስርዓት የዚያው ቅጥያ ነው።የእኛዎቹ አምባገነንና ሕገወጥ ቡድኖች ከሌላው አገር አምባገነኖች የሚለዩበት ቢኖር አገር ጠል መሆናቸው ነው።አንዳንዶቹ አምባገነኖች የሕዝቡን መብት የነፈጉ ቢሆኑም ስለአገራቸው አንድነትና ልዑላዊነት ጠንካራ አቋም ስለሚኖራቸው ይኸው አቋማቸው ለሥልጣን መውጫ መሰላል ሆኖ ተጠቅመውበታል። የኛዎቹ ሁለቱንም ጸባዮች የተሸከሙ ጉዶች ናቸው።ለአገር አንድነት ደንታ የላቸውም፣ይባስ ብሎም የሚመሩበት መመሪያ አገር የምትፈራርስበትን መንገድ የሚጠርግ ነው። ለሕዝቡም አያስቡለትም፤በጎሳ ተከፋፍሎ ፣ቋንቋና ሃይማኖት ለይቶ እርስ በርሱ እዬተጋጨና እዬተጨፋጨፈ እንዲያልቅ፣በጠላትነት ሰልፍ ውስጥ እንዲገባ አድርገውታል።

በሕገወጥ መንገድ ሥልጣኑን ይዞ መንግሥት ነኝ የሚል ቡድን ለሕግ ጸርና ጠላት ነው።የሚያደርገው ሁሉ ሕግን ወይም ፍትሕን የሚከተል አይደለም።ለሱ ሕግ ማለት ጉልበትና ማሸበር ነው።ይህንን የሚያስፈጽሙ የራሱ የሆኑ አካላት አሉት።በፍርድ ቤት ወንበር ላይ ተቀምጠው የሚፈልገውን ውሳኔ የሚሰጡ ጥቁር ካባ ለባሾች ዳኞች አንላቸውም፣ምክንያቱም ዳኝነት ከባድ አላፊነትንና የህሊና ብቃትን ስለሚጠይቅ በመሆኑ።የዚያው ተባባሪ የሆኑ ካለፍርድ እያፈሱ በዬእስር ቤቱ የሚያጉሩና የሚያሰቃዩ ሕግ አስከባሪና ፖሊስ በሚል ጭንብል ያጠለቁ አረመኔዎች የሕገወጡ ቡድን የዕድሜ ልክ አሽከሮች ናቸው። እነዚህ ሦስቱ እጅና ጓንት ሆነው የፈረደበትን ሕዝብ እንዳሻቸው ይነዱታል።

እነዚህን መሣሪያ በማድረግ ከሚፈጽሙት ወንጀል ጋር የሚጣጣም የውሸት ናዳ እያዘነቡና ባዶ ተስፋ እዬቀለቡ ሕዝቡን ለማጃጃል የማያደርጉት የለም። ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ በሚመስል መልኩ ሳይበላ እንደጠገበ ፣ሲያዝንና ሲመረር እንደ ደላው በማውራት የማያውቀውን ዓለም በተስፋ ያሳዩታል።ይህንን ባዶ የቃላት ጋጋታ የማይቀበለውና ገሃዱን ሁኔታ ደፍሮ የሚያጋልጠውን እያሳደዱ መግደልና ማሰር አንዱ የሥልጣናቸው ማሳያ አድርገውታል።በጉልበት ሕግ አውጭ፣አስተርጓሚና አስፈጻሚ የሆኑት እነዚህ ቡድኖች ሕግን ወይም ፍትሕን መቀለጃቸው ብቻ ሳይሆን የቅጣት በትራቸው ካደረጉት ዓመታት አልፈዋል።በሰሞኑ ግን የታዬው አያድርስ ነው።

ከሶስት ወራት በፊት ምንም ሳያደርጉ በአፋኞች ታፍነው ከመሥሪያቤታቸውና ከመኖሪያቸው የተወሰዱት ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ድርጅት አባላት የገቡበት ሳይታወቅ ቆይቶ በቤተሰብ ፍለጋና በሕዝብ ጩኸት ያሉበት ቢታወቅም የሰሩት ወንጀል ሳይታወቅና ለይምሰልም ቢሆን ሥርዓቱ ባቋቋመው የካንጋሮ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለወራት በጨለማ ቤት ቆይተዋል።ከብዙ ውጣ ውረድና በጠበቆች ድካም በሥርዓቱ ፍርድ ቤት ቢቀርቡም ወንጀላቸው በማስረጃና በምስክር ሳይረጋገጥባቸው የብዙ ሽህ ብር ዋስትና ተፈርዶባቸው እንዲለቀቁ ቢበዬንም እዛው በዛው በሆነው የሥርዓቱ የሕግ አስከባሪውና አስፈጻሚው የጀርባ ስምምነት ገንዘቡን ከከፈሉ በኋላ ሳይለቀቁ በነበሩበት እንዲቆዩ ተደርጓል።

ከሕግ በላይ የሆነው የሕገወጡ አምባገነን ቡድን መሪ እንደፈለገ በክስ ላይ ክስ እዬደረደረ እንዳይለቀቁ ማድረጉን ቀጥሎበታል።ተመስገን ደሳለኝ ብዙ መቶ ሽብር ከፍሎ አሁንም አልተለቀቀም፤ቢለቀቅ እገለዋለሁ የሚልም መከላከያ የተባለ ተቋም በአደባባይ ሲዝት መስማቱ የሥርዓቱን ምንነት በግልጽ ከማሳዬቱም በላይ ምን ያህል እብሪተኛ ሥርዓት እንደሰፈነ ማረጋገጫ ነው።የሌሎቹም ጋዜጠኞች አፈና እንዲሁ ሕገ ወጥ ነው። በህጻናት ልጆቹ ፊት ከቤቱ የተወሰደው አዛውንቱ ታዲዎስ ታንቱ፣ ከገበያ መሃል የታፈነችው የህጻን ልጅ እናት የሆነችው ማእዛ ሞሃመድና ጋዜጠኛ አሳዬ ደርቤ የገንዘብ ዋስትና ከፍለው እንዲለቀቁ ቢፈረድባቸውም፣ተፈረደላቸው አንልም ምክንያቱም ሲጀመር መታሰራቸው በራሱ ሕገወጥና ተገቢ ስላልሆነ ነው። እንዲከፍሉም የተጠዬቁት ገንዘብ ከዘረፋ ጋር ስለሚመሳሰል ነው።ሆኖም ግን ገንዘቡን ከከፈሉ በኋላ በፖሊስ እምቢባይነት ከእስር ሳይለቀቁ ቆይተዋል።ንበዜ ሲሳይም በገንዘብ ዋስትና ይፈታ ከተባለ በኋላ ለእንግልት ተዳርጎ ለዳግመኛ ፍርድ የክስ መዝገብ እዬተረቀቀበት መሆኑ ተሰምቷል።በሱ ላይ የቀረበው ክስ ለወያኔ ሰላይና ተላላኪ፣መንግሥትን የሚያወግዝ፣ በሃሰት የሚከስና ለማሶገድ ሴራ ላይ የተሳተፈ የሚል ሲሆን ለረጅም ጊዜ ለማሰር የሚያስችል ተደርጎ ነው።የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲም አመራር አባል የሆነው ስንታዬሁ ቸኮል ለተከሰሰበት ወንጀል ማስረጃና ምስክር ሳይቀርብበት ከመቶ አርባ ሽህ ብር በላይ በተለያዩ የሥርዓቱ ዳኞች ተፈርዶበት ገንዘቡን ከከፈለ በኋላ ፖሊስ አለቅም ብሎ ከክልል ክልል እስርቤቶች እዬተቀያዬረ ይባስ ብሎ በማይኖርበት ክልል በኦሮሚያ ቡራዩ እስር ቤት ተወስዶ ካለፍርድ መንገላታቱ ሳያንሰው ባደረበት ህመም የሕክምና እርዳታ ተነፍጎት እዬተሰቃዬ ቆይቷል።በሁሉም ላይ ለተከሰሱበት ወንጀል የቀረበ ምስክርም ሆነ ማስረጃ የለም።እንዲፈቱ ያዘዘው ፍርድ ቤት ተከሳሾቹ ባለመፈታታቸው ፖሊሱን ለምን አልፈታህም ብሎ ሲጠይቀው ምክንያቱን ለማስረዳትና መልስ ለመስጠት አልቻለም። ይህ የሚያሳዬው እስራቱም ቅጣቱም ከበላይ አካል በቀጥታ ከቤተመንግሥት የሚመጣ መሆኑን ነው። አብይ አህመድ ሕግም፣ዳኛም ሆኖ ያሻውን እያደረገ ለመሆኑ ከዚህ በላይ ማስረጃ አይኖርም።

ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ከአራት ቀናት በፊት ማዕዛ ሞሃመድና አሳዬ ደርቤ የተለቀቁ ሲሆን፤ ስንታዬሁ ቸኮልም በጥቅምት 5 ቀን 2015 ዓም ተፈቶ ከቤተሰቡ ጋር መቀላቀሉ ተሰምቷል። አሁን

በእስር ላይ የሚገኙት ተመስገን ደሳለኝ፣ታዲዎስ ታንቱና ጎበዜ ሲሳይ ሲሆኑ እጣ ፈንታቸው ገና አልታወቀም።

ለሥርዓቱ አደጋ የሆነበትና እንቅል የነሳው የአማራው መነሳሳትና የፋኖ አደረጃጀት ነው።ይህንን የሕዝብ መነሳሳት ለማፈን በፋኖነት የተደራጁትን የአማራውን ልጆች እያደኑ ማሰርና ማሳደድ የለት ተለት ተግባሩ አድርጎታል።በአዴን በተባለው ተላላኪ ድርጅት በኩል ብዙ የአማራ ልጆች ተገለዋል፣ ቆስለዋል፣ ታፍነዋል።እንደ ዘመነ ካሴ ያሉትም መሪዎች በሽምግልና ስም እንዲቀርቡ ተደርጎ ለእስራት ከተዳረጉ ሳምንታት አልፈዋል።ባልፈጸሙት ወንጀል ከሶ ከፍተኛ ቅጣት ለመጣልና በአማራው ፋኖ ትግል ላይ ውሃ ለመቸለስ የሚደረገው ዝግጅት ተጠናክሯል።ቀጠሮው ቀጠሮ እዬወለደ ከሕዝብ ነጥሎ ለማቆዬት የሚሸረበው አሻጥር ቀላል አይደለም።ያም ሆኖ ግን ትግሉን ያጠናክረዋል እንጂ አያዳክመውም።በአንድ ፋኖ ወይም በጥቂት ፋኖዎች ላይ በሚደርስ የበቀል እርምጃ የብዙሃኑ ትግል አይቆምም።የብዙሃኑ ትግል እንዲሰምር፣የሕዝቡ ልጆች እዬታፈኑ እንዳይወሰዱ የሚከላከል ድርጅትና ሃይል መፍጠር ለነገ የማይባል ተግባር ነው። ፍትሕ በትግል እንጂ በልመና አይገኝም።

የብልጽግና መራሹ ፍርድ ቤት ፍትሕ በትክክል የሚተረጎምበት ቦታ ሳይሆን የጠሉትን የሚቀጡበት ዱላ ከሆነ ውሎ አድሯል።በቀድሞ ጊዜ ሲሰራበት የኖረው በሰው ዋስትና የመልቀቁ አሠራር በገንዘብ ዋስትና መለወጡን ስናይ ፍርድ ቤት የገንዘብ መሰብሰቢያ የገበያ አዳራሽ ሆኗል ከማለትም በተረፈ ሥርዓቱ ዘራፊ ነው ለማለት እንደፍራለን።ለዚያም ነው ሁሉም ነገር ለሽያጭ የሚቀርበው።የከተማ ቦታ ለሽያጭ፣ባንክ ቤት ለሽያጭ፣ቴሌ ለሽያጭ፣የማዕድን ቦታ ለሽያጭ፣ነገ ደግሞ የአባይ ግድብና የኢትዮጵያ አዬር መንገድ ለገበያ እንደማይቀርቡ ዋስትና የለም።በመሸጥ በመለወጥ ገንዘብ መሰብሰብ ቀዳሚ ዓላማው ያደረገ የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ቡድን አገርም ቢሆን ከመሸጥ አይመለስም። የመንግሥትን ገንዘብ ሰብሳቢነት እንደ አርአያ ተከትለው የሚዘርፉ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ተቋማትም እንደ አሸን ፈልተዋል።ንብረትና ቦታ ብቻም ሳይሆን የሰው እሬሳም የሚቸበቸብ ሸቀጥ ሆኗል።በሰሞኑ በጋዜጠኞች የወጣው ጉድ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው።በጳውሎስ ሆስፒታል ውስጥ የሞቱ ሰዎች አስከሬን ለተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለትምህርት ተብሎ እስከ 60 ሽህ ብር ድረስ እንደሚሸጥ የሸጠው የጳውሎስ ሆስፒታል ዶክተርና የገዙት ዩኒቨርሲቲዎች ሳይቀሩ የእምነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፤ አንዳንዶቹም ከወንጀሉ የራቁ መስሏቸው ለመስጠት ፈቃደኞች አልሆኑም። በዚህ ጨረታ ገበያ ላይ የሚቀርቡት ዘመድ የሌላቸው ብቻም ሳይሆኑ ቤተሰብ ያላቸውም ጭምር እንደሆኑ የዘመዳቸውን አስከሬን የተነፈጉት እያለቀሱ የተናገሩት የድምጽ ቅጂ ተላልፏል።

በሌላው አገር ለጥናትና ምርምር ሲባል የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ በራሱ ወይም በቤተሰብ ፈቃድ የሰውነት አካሉን መስጠት የተለመደ ነው።በእኛ አገር ግን ልጆችና ጎዳና ተዳዳሪዎች ለኩላሊትና ለሌላ ጠቃሚ የሰውነት ክፍል ቅያሪ ሲባል የገቡበት ሳይታወቅ መቅረታቸው ያደባባይ ምስጢር ነው። እንዲህ ነው ጨካኝና ገንዘብ ወዳድ፣ዘራፊና ሌባ ሥርዓት በሰፈነበት አገር የሚርመሰመሱት ለሃቅ የቆሙ ሳይሆኑ በሙታን በድን አካል ንግድ ላይ የተሰማሩትን ጨካኝና ሆዳሞችን ጭምር ነው። ሥርዓቱ ካልተወገደ በቀር በዚህ መስክ ላይ የተሰማሩበት ወንጀል ባህል ሆኖ ይቀራል።ሁለገብ ውድቀት ማለት እንዲህ ነው።በሁሉም አቅጣጫ ገንዘብ ከሰው ልጆችና ከአገር በላይ ሆኖ ዘራፊ የሚወደስበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

ኦነግ መራሹ ኦሕዴድ ብልጽግና የኢትዮጵያን ሕዝብ በተለይም አማራውን ገንዘቡንም፣ማንነቱንም፣ የሚኖርበትን አገሩንም ነጥቆ ባዶ እጁን እንዲቀርና የበይ ተመልካች እንዲሆን ፈርዶበታል።የኦነግ ቤተሰብ የሆነው አንዱ ኦፌኮ የተባለው ጸረ ኢትዮጵያ ድርጅት የአዲስ አበባ ሕዝብ ለኦሮሞ ክልል ካሳ ይክፈል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ፣ የኦሕዴድ ከንቲባዋ ተቀብላ አዲስ አበባ ላለፉት 28 ዓመታት

ለኦሮሞ ክልል ካሳ እንዲከፍል መስማማቷ በሚዲያ ተገልጿል።አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ ይሏል ይህ ነው። ለምን 28 ዓመት ቢባል ላለፉት አራት ዓመቶች ኦነግ ኦሕዴድ ስለሆነ የሥልጣኑ ባለቤት ኦሮሞ ለኦሮሞ አይከፍልም ወይም የከፈለው ከግምት ውስጥ በመግባቱ ምክንያት ሳይሆን እንደማይቀር እናምናለን።ይህ የአዲስ አበባን የመሰልቀጡ ሂደት የመጨረሻው መጀመሪያ እንደሆነ ማሳያ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአዲስ አበባ ነዋሪ በቤት ኪራይና በግብር የማይችለውን እዬተጠዬቀ ከሥራው ሲፈናቀል በቦታው የሚተካው፣ቤቱም ሥራውም ለሥርዓቱ ጎሳ ተወላጅ መሆኑ ጸሃይ የሞቀው አገር ያወቀው ሃቅ ነው።ሁሉም ነገር የእኛ የሚለው ድፍረትና ስግብግብነት በገሃድ ታይቷል፤ እዬታዬም ነው፣ሕዝቡ በዓይኑ እያዬና፣ጉዳቱንም እዬቀመሰ ተደጋግሞ የሚሰጠውን ምክርና የማስጠንቀቂያ ደወል ካላዳመጠ፣ማድረግ የሚገባውን ሳያደርግ ቀርቶ በፍርሃት ድባብ ውስጥ ከተቀመጠ፣ ለሚደርስበት መከራ ተጠያቂው እራሱ ብቻ ነው።ይሉኝታ ቢሱ ኦነግ ኦሕዴድ ግን ኢትዮጵያን ከማፍረስና ኦሮሚያ የሚባል በታሪክ ያልነበረ አገር ከመፍጠር ዓላማው ዝንፍ አይልም። ዝንፍ ሊል የሚችለው የሚያዛንፈው ኢትዮጵያዊ የሆነ ሕዝባዊ ሃይል ሲፈጠር ብቻ ነው።

ከጎሰኝነቱ በተጨማሪ ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የሚታወቅበት ሌላው ገጹ ውሸትና ክህደት ነው። ኢትዮጵያ በርሃብ ምክንያት ከውጭ አገር የእህል ሸመታና እርዳታ ሳትወጣ እራሷን ችላ፣ከሕዝቧ ተርፎ ለውጭ አገራት ስንዴ ትልካለች የሚለው የአብይ አህመድ ቅዠት (ፋንታሲ)ና ውሸት ዓለምን ፈገግ አሰኝቷል።ቢሆን መልካም ነበር፤ ግን በተራበው ሕዝብ ላይ መቀለድ ብቻ ሳይሆን ለምኖ እርዳታ እንዳያገኝ የሚያከላክል ጭካኔ የወለደው ውሸት ነው።በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ለኢትዮጵያ እህል ከሚሸጡት አገሮች መካከል አንዷ ግብጽ መሆኗ ነው።ካሮትና ዱላ የሚባለው የተጽእኖ ፖለቲካ ትርጉም የሚያገኘው እዚህ ላይ ነው። የአባይ ግድብ የግብጾችም እጅ አለበት የሚለው ጥርጣሬ የሚነሳው ከባዶ ሜዳ ላይ አለመሆኑን በንግዱ ዚሪያ የሚደረገው መቀራረብ ያሳያል።

የሰሜኑን ጦርነት በተመለከተም መፍትሔ እንዲያገኝ አይፈለግም።በተራዘመ ጦርነት ወያኔ ከምዕራባውያን በተለይም ከአሜሪካ የሚያገኘው እርዳታ በቋሚነት እንዲቀጥል ይሻል።ጦርነቱ መፍትሔ ካገኘ ያ ሁሉ ጥቅም ሊቀር ነው።ከዛም በላይ በችግር የሚኖረው ሕዝብ ጥያቄ ሊያነሳና ሊያምጽ ይችላል።ስለዚህ በስበብ ባስባቡ ውጊያውን ከማካሄድ የተሻለ ምርጫ የለም።ኦነግ- ኦሕዴድ ብልጽግናም በበኩሉ ጦርነቱን ሰበብ በማድረግ እራሱን በአገር ወዳድነት ለማሳዬትና ለማዘናጋት ይጠቀምበታል።በተጨማሪም አማራው መድቀቅ ስላለበት ከባቢው ከጦርነት የጸዳ እንዲሆን አይፈለግም።የሁለቱም ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑት መደራደሪያቸው የአማራው መብትና መኖር ጥያቄ ነው። በድርሻ ከተስማሙ በጋራ ዓላማቸው የማይስማሙበት ነገር አይኖርም።በአማራው ኪሳራ ከመደራደር አይመለሱም።የራያና አዘቦ፣የወልቃይትና ጠገሌ ለም መሬቶችም የስምምነት ገጸ በረከት ሆነው በሕገመንግሥቱ ተብዬው ሽፋን ይቀርባሉ።

በተለያዩ ትርምሶች ውስጥ የምትናጠው አገራችንና ሕዝቧ በውዥንብር ውስጥ እንዲቆዩ የአብይ አህመድ ቅጥረኛ ጋዜጠኞች የሚነዙት የተምታታ ጫጫታ መያዣ መጨበጫ የለውም። የመከላከያ ሃይል አክሱምን አልፎ መቀሌን ከበበ፣የወያኔ ሃይል ድባቅ ተመታ፣መሪዎቹ ፈረጠጡ፣ግማሾቹም ሞቱ፣ ቆሰሉ፣ተማረኩ የሚል ወሬ ሲያናፍሱ፣ የወያኔ አፈቀላጤዎች በበኩላቸው ይህን ያህል ጦር ደመሰስን፣ ማረክን፤ ቆቦንና ከባቢዋን ተቆጣጠርን የሚል ወሬ ይነዛሉ።ወሬም ሳይሆን የከባቢው ሕዝብም ይህንኑ ያስተጋባል።በመካከሉ ሕዝብ ሰላም አጥቶ ለወከባ ኑሮ ተጋልጧል፤ይህ በሁለት ጸረሕዝብ ሃይሎች መካከል በስምምነት የሚደረግ የጦርነት ቁማር ነው ለማለት ያስደፍራል።

የአሜሪካ ተላላኪ የሆነው ዲፕሎማት ማይ ሃመር አዲስ አበባና መቀሌ እግሩ እስኪቀጥን የሚመላለሰው ያንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ነው። ለሰላም ድርድሩ ሲል መምጣቱ ቢነገርም፣የደቡብ

አፍሪካው ድርድር ሳይጀመር ተጠናቋል። በሎጂስቲክስ ምክንያት አልተካሄደም የሚለው ትርክት ውሃ አይቋጥርም።አሜሪካና አውሮፓን ያህል አገሮች የሚያሸከረክሩት ድርድር በሎጂስቲክስ ምክንያት ከመደረግ ሊታገድ አይችልም።እስከሚገባን ድረስ ሎጂስቲክስ ማለት ፣የመሰብሰቢያ ቦታ፣የመጓጓዣ፣ የማረፊ፣ድርድሩን የሚመራ አካል፣የደህንነት ዘርፍ ብቃት ሲሆን ለነዚህ ወጭዎች የሚሆን ፈቃደኛና ገንዘብ መኖር ማለት ነው።ከዚያ ውጭ ተደራዳሪዎቹና አደራዳሪዎቹ የማይስማሙበት አካሄድ ካለ፣ በሰዎቹ ወይም በአጀንዳ ቀረጻ ሊሆን ይችላል ስምምነት ከሌለ ድርድሩ ሊካሄድ አይችልም። ቦታው፣ አደራዳሪዎቹና ተደራዳሪዎቹ ከተገለጹ በኋላ ድርድሩን አለማካሄድ ግን በሎጅስቲክስ ሊሆን አይችልም።አንዱ ታዛቢ የነበረው የኢሁሩ ኬንያታም ማፈግፈግ አንድ የተደበቀ ምክንያት እንዳለ ለመጠርጠር ያስችላል።

ይህ በእንዲህ እያለ ኦነግ ኦሕዴድ በሌላ ክልል የሚያደርገው የመሬት ነጠቃውን አፋፍሞታል።የመሬት ነጠቃው በጦርነት መታጀቡን ደጋግመን ታዝበናል።በሶማሌ ክልል ውስጥ ያሉ ቦታዎችን ለመያዝ ጦርነት ከፍቶ ብዙ ሰዎች ተገለዋል።በደቡብ ክልልም እንዲሁ።ሁሉ አማረኝን ገበያ አታውጧት እንዲሉ ሁሉንም ካልበላሁ የሚል የራበው ጅብ ሆኗል።ለመውረርና ለመንጠቅ ያልቋመጠበት ክልልና ዞን የለም።መሬት ብቻም ሳይሆን ታሪክ የመሻማትና የመንጠቅም አባዜ ተጸናውቶታል።ቅርሶችን የማውደም ዘመቻም አንዱ መገለጫው ሆኗል።

የአገሪቱን ገጽና ታሪክ ለማጥፋት ከሚያደርገው ዘመቻ ጎን ለጎን እራሱን ባለታሪክ ለማድረግ የሚያደርገው መላላጥ የሚያስቅ ቢሆንም የጅልነቱና የድፍረቱ መጠን ሲታይ ወግድ ሊባል የሚገባው ነው እንላለን።ኦነግ ኦሕዴድ የሚፈጽመው ሁሉ ሌላውን ቀና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ኦሮሞ የሃፍረት ማቅ እያለበሰው ነው።የኦነጉ የስፖርትና የባህል ሚኒስትር ቀጀላ መርዳሳ የሰሞኑን የሙስሊም የመውሊድ በዓል ምክንያት በማድረግ በሙስሊሞች ፊት ቀርቦ የኢትዮጵያ መሪ የነበረውን ባህረነጋሽ የነብዩ ሞሃመድን ተከታዮች ተቀብሎ ያነጋገረው በኦሮምኛ ቋንቋ አቻም በማለት ነው ሲል፣የሱ ተከታዮች ደግሞ ምን እሱ ብቻ አውሮፓውያንም ኦሮምኛ ነበር ቋንቋቸው ለምሳሌም ጣሊያኖች እንዲያሞ የሚሉት ኢንዲሞ የሚለውን የኦሮሞ ቃል ወስደው ነው ይላሉ።በዚህም አይቆሙም፤ ጣሊያኖችም ሆኑ ሌሎቹ ቢራ የሚባለውን መጠጥ አጠማመቅ የወሰዱትና የሰዩሙት ከመጀመሪያው ጠማቂ ከሆነው የኦሮሞ ተወላጅ ቢራቱ ነው የሚል ትርክት ይዘው ብቅ ብለዋል። ኦሮምኛን በርዘው በራርዘው አዳከሙት፣የላቲን ፊደልም የኛው ስለነበር አሁን ብንጠቀም አያስገርምም ይላሉ።ከመገረም ያለፈ ሳቅ ይዞን ነገ ደግሞ ምን ይሉ ይሆን ብለን ለመሳቅ በጉጉት እንጠብቃለን።ጅል አይሙት እንዲያጫውት!

በዚህ አይነት ድፍረትና ድንቁርና ብሎም ይሉኝታ ቢስነት ባሕር ውስጥ የሚዋኘው የኦነግ-ኦሕዴድ ብልጽግና ያሻውን ሲያደርግ በዝምታ ማለፍ በአገራችን ውስጥ ሰው የለም ወይ ያሰኛል።ሰው ስንል በሁለት እግሩ ቆሞ የሚሄድ ማለታችን ሳይሆን ስብእና ያለው፣ለሙብቱ የሚከራከርና የሚታገል፣ለአገሩ ክብርና ልዑላዊነት የሚቆም ማለታችን ነው።እርግጥ ነው ጥቂቶች መስዋእት መክፈላቸው አይካድም፤ ግን የሚታገሉት በተናጠል በመሆኑ የእሳት እራት ከመሆን አላመለጡም።ለዚያም ነው ደግመን ደጋግመን ትግሉ በድርጅት ይመራ የምንለው።

አሁንም እንላለን የተበታተነውን ሕዝባዊ ትግል የሚያቀናጅና የሚመራ ድርጅት መቋቋም አለበት።አገር አጥፊዎቹ ጎሰኞች ተደራጅተው ያሻቸውን ሲያደርጉ እያዩ በዝምታ ማለፍና የመከራ ሰለባ መሆን የለበትም፤ ስለሆነም ሌላው ብዙሃኑ አገር ወዳድ እራሱንም አገሩንም ከጥፋት ለማዳን የግድ መደራጀትና መሰባሰብ አለበት የሚለው የዘወትር ጥሪያችን ነው።በተለይም የአዲስ አበባ ሕዝብ

ተደራጅቶ መብቱን ካላስከበረ፣የከተማዋ ባለቤትነቱን ካላረጋገጠ በቀጣዩ ሊደርስበት ከታሰበለት እልቂትና መፈናቀል ሊያመልጥ አይችልም።

የኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ያንድነት ግንባር ይመስረት!

አንድነት ሃይል ነው!!